# ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!

*በስመ አብ፤ ወወልድ፤ ወመንፈስ ቅዱስ፤ አሀዱ አምላክ፤ አሜን።*

## *የሰመርናሃ ሰፋሪዉ አባ መላኩ(ፋኑኤል) በህግ አምላክ በሰንደቅ አላማዉ !!!*

*የጉዳየ መነሻ ሰሞኑን በዋሽንግተን ዲሲ፤ በቤተ ክርስቲያናችን ዙሪያ በውስጥና በውጭ የሚካሄደውን አየሁ። የሚንጫጫውንም ሰማሁ።በተለይም በተሳሳተ መረጃ በቦታዉ በመገኜታቸዉ የሚከነክናቸዉን ሁለት ምሁራን ዶ/ር ወገኖችና የእህቴ የዚያ የአገር ኩራት የጀግናዉ ኮረኔል አብዲሳ ኢጋ ልጅ የነገሩኝን ቁጭት አዳመጥኩ፤ በዚህም ፥*

*ድንበር እያፈረሱና ህዝቡን በጎሳና በቋንቋ እየከፋፈሉ፤ እርስ በርስ በመጠራጠር እያጣሉ በአልጠግብ ባይ ስግብግብ ባህርያቸው የቀረውን የኢትዮጵያ ህዝብ ከያለበት ከኖረበት ከተወለደበት፤ ስላአፈናቀሉት። ለዘረፉት፤ንብረት አልባ ቤት አልባና ቀየ አልባ ላኢደረጉት እርመኞች እነ ነውር ጌጡ ለእርመኞች ሲያላዊ መቅሰፍት ህጋዊ ፈቃድ የሰጡበት ድራማዊ ትያትር፤ በህግ አምላክ በሰንደቅ አላማዉ !ቤተክርስትያንን ኢያዋርዱ ለማት ፈቀድኩ ።ይህም ቤተክርስትያንን አመድ አፋሽ ያደረገ በሰመርናሃ ሰፋሪ በአባ መላኩ (ፋኑኤል) በዋሽንግተን ዲሲ ቤተክርስትያን ለአሳዳጆች የ1600 ኪሎ ሜትር የሚረዝመውና ስፋቱ እስከ 50 ኪሎ ሜትር የሚደርስ የኢትዮጵያ (መተማን )ለም መሬት ለባእዳን አገር ለሱዳን ከእነ አባይ ስኳሬ ጋር ሆኖ አገር አልባ ስላደረገን ለካሳ ተ/ብርሀን የተከናወነዉ ፤የቤክርስትያን የቀኖና ዕቃ ፤ሽልማት ለም መሬቱን እየተነጠቀ ከአባቶቹ ምድር ለተሳደደው አማራ ኢትዮጵያዊ ጥያቄ? በማስነሳቱ ነዉ ። እንደሚታወቀዉ ቅድስት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን ለተፈጥሮም፤ ለሰውም የምትሰጠው ፍቅር ሰማያዊ ጸጋዋ ነው የሚል ሙሉ ዕምነት አለኝ። ሃይማኖታችን ሰብዕዊም፣ ተፈጥሯዊም ናት። ብሄራዊም፣ ዓለም- ዐቀፋዊም ናት። ስለሆነም እግዚአብሔር ለፈጠራቸው ፍጥረታት፤ ነፍሳት፤ የተፍጥሮ ጸጋዎች፤ ምድርና ሰማይ፤ ጋራው እና ሸንተረሩ፤ ወንዝና ወቅያኖሱ፤ ሃይቃትና ሸለቆው፤ አዝእርቱ እና እጽዋቱ፤ ንፋስ እና አየሩ፤ ሙቀት እና ቅዝቃዜው፤ ወቅታት እና ዘመናት፤ ማዕልትና ግርማ ሌሊቱ ሁሉ በተፈጠረላቸው ሥነ ምግባር መሰረትነት በሰላም ውለው ያድሩ ዘንድ፤ ለኢትዮጵያና ለዓለም ተግታ ትጸልያለች ። በርትታ ትፆማለች፤ ባልተቋረጠ ሁኔታ ትሰግዳለች፤ በተከታታይ ምህላ ትይዛለች፤ አቅዳም ሱባኤም ትቆጥራለች። አምላኳንም ተግታ፤ በጥንካሬና በብርታት ታመሰግናለች። ቤተክርስትያን አላማዋ የሰዉን ፍጥረት በፍቅር የምታቀርብ ለሚያሳድዱአት የምትጸልይ የማታርቅ ስትሆን ከጨለማ ጋር ግን ህብረት የላትም። የእግዚአብሔር ቃል "ብርሃንም ከጭለማ ጋር ምን ህብረት አለዉ?" ቆሮ-6፥ 14 እንዳለ ፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያንም ከጭለማ ጋር ግን ምንም ህብረት የሌላት በመሆኑ ከአመጽ ጋር ተካፍለዋልና የሰመርናሃ ሰፋሪዉ አባ መላኩ(ፋኑኤል) በማለት ሀሳቤን አስቀመጥኩ።*

*እንዲህም ሆነ፣ የሰመርናሃ ሰፋሪዎች :- እስራኤል በባቢሎን ለሰባ ዓመታት በባርነት ከሚኖርበት ግዞት ሊወጣ ሲቃረብ ነብዩ ኤርምያስ እስራኤላውያን ጣዖትን ከሚያመልኩ ባቢሎናውያን ጋር ጋብቻን እንዳይፈፅሙ፤ የፈፀሙትም እንዲያፈርሱ ያስተምር ነበር። ጣዖት አምላኪዎች ወደ ተስፋይቱ ምድር እንዳይገቡ የተከለከለ ነበርና። ጊዜው ደርሶ እስራኤል ወደ ኢየሩሳሌም ሲመለስ ኤርምያስና የጎበዝ አለቆቹ በኢየሩሳሌም በር ቆመው ከባቢሎናውያን ጋር የተጋቡትን እንዳይገቡ ከለከሏቸው። ከባቢሎንም*

ከኢየሩሳሌምም የተባረሩት እነዚህ ሰዎች እግራቸው ወደመራቸው ሲጓዙ አንድ ስፍራ አገኙ። በዚያም ሰፈሩ። የቦታውንም ስም ''ሰመርናሃ' ብለው ጠሩት፥ በኋላም ያ ስፍራ ሰማርያ ተባለ። የሰማርያ ሰዎች በወገኖቻቸው ላይ ክህደትን ፈጽመዋልና፤በባርነት ካስገበሯቸው ባቢሎናውያን ጋር ተዛምደዋልና ከጣኦት አምላኪዎች ጋርም ተጋብተዋልና በአይሁድ ዘንድ እጅግ የተናቁ ነበሩ። ዛሬም እንዲሁ በእኛ በኢትዮጵያዉያን ምንዱባን ዘንድም እርመኞች ጋር ክህደት ፈጽመዋልና የቀለሉ ጨለማ ሆነዉ አይቻለሁ የሰመርናሃ ሰፋሪዉ አባ መላኩ(ፋኑኤል) ። አየ አባ፤ ስንቴ ይበድሉን ፥ለቁጥር አታካች ነዉ የሆነው። ምናምንቴ ብለው ከጥላዎት ፈጥነው ከምናምንቴ ጋር በመቡዋደን ሪከርድ በጥሰዋል።

እዉነት ፥ እናታችን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን መጽሐፍ “ብርሃናችሁ በሰው ፊት ያብራ” እንዲል በዚህ ምድር የመኖሩ ዓላማ ገብቶአቸዉ ቅዱሳን በዘመናቸው ዘመን የማይሸረው ሥራ ሰርተውና ቅርስ ትተውልን እንዳለፉ ሁሉ የእነኛን ቀደምት አባቶች እግር የሚተካ አባት በአሚሪካ የምትመድበዉ የሊቅ ደሀ ሆነችን ? ምሥጥሩ ምንድን ነው?።

''በመደመር ስም “ የእርመኝነት ንግድ ይቁም! እንቃወማለን፤ዛሬም ሆነ በኢሳቱ ጋዜኛ ሲሳይ አጌና ምናልባትም ከሰባት አመት በፊት በሰራዉ ዘገባ ካሳ ተ/ብርሀን የሚባል ? ኣስታራቂ አይተንም ሰምተንም አናቅም ።የምን ግርግር ለምን ያመቻል ካልተባለ በቀር፤። በዚህ የእርቅ መጀመሪያ ቀደምት የኮሚተ ምስረታ ሂደት ቅንነት ያልተነገረለትን መምህር ዘበነ ለማን ቢሸልሙት ኖሮ ምንኛ ባማረብዎት ነበር ። ዳሩ ግን መሰረቱን ስለማያዉቁት ስህተት ቤቱ አድርጎዎታል ።ለአስራ ሶስት አመታት ለቤተክርስትያን እርቅ የደከምነዉ፥ ለእኔ ቅድስት ሃይማኖታችን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ዕምነት ብቻ ሳትሆን፤ የአገር እና የህዝብ ቀስተዳመና ናት ብዬ አምናለሁ። ይህም ብቻ አይደለም፤ የቅድስት ኦርቶዶክስ ሃይማኖት ቅኔ የሚገለጠው በሰው እና በተፈጥሮ መካከል ሊኖር የሚገባውን የሰመረ ግንኙነት አንባቢ፤ ተርጓሚ፤ አማሳጣሪ በመሆን ብቻ ሳትሆን፤ በተጨማሪም አስማሚ፤ አግባቢ፤ ዳኛ እና ችሎትም ሚዛን ም ናት ፤ ታሪክ የማይሸራት ቅድስት ፤የፍቅር ሰማያዊ ጸጋ ናት።

ለእኔ በመደመር ፤ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፤የቤተክርስትያን ኣባቶች በሲኖዶሳዊ ሰላምና እርቅ ፤የሰላምና እርቅ የእርቅ ቀን ። ያ የመከፋት ምጣድ ዘመን ሰቆቃው፤ የቆይታ ጊዜ ተደመሰሰ። በፍቅር ማሸነፍን (1ቆሮ. 1፡10-15) በመከፋፈል መንፈስ ሆነው የጎሪጥ የሚተያዩትን የእናት ቤተክርስቲያን ልጆችን ወደ አንድነት እናመጣቸው ዘንድ “በአንድ አሳብ ተስማሙ፥ አንድ ፍቅር፡ አንድም ልብ፡ አንድም አሳብ ይሁንላችሁ” የሚለውን የሐዋርያውን መልዕክት የአገልግሎት መሪ ጥቅስ ለመፈፀምና፤ መደመር መንፈሳዊነትን ከሰው ልጆች ነፃነት ጋር ያጣመረ፣ ያቀናጀና ያስተሳሰረ ምስክር እንዲሆን በኢትዮጵያ እንጂ ፤ ወገኖቻችንን ሀገር አልባ፥ በማድረግ በግፍ እንዲጨፈጨፉ ምክንያት ከሆነ እርም ጋር በቀላሉ የማይፋቱት ጋብቻ ፈፅመው ፤በመሰሪ ተግባራቸው ከምድራችዉ በማፈናቀል ፤ ወገኖቻችንን ለማጥፋት ሲጠቀሙበት በተባባሪነት መሸለም ለቤተክርስትያኔ ዕዳ፥ ለትውልዴም ማፈሪያ እንዲሆኑ አልነበረም። በዚህም ምክንያት የሰመርናሃ ሰፋሪ አባ መላኩ (ፋኑኤል)ለእርመኝነት ሲያላዊ መቅሰፍት ህጋዊ ፈቃድ ካባ ሸላሚነት ፤ ኢትዮጵያዊዉ ወገናችን የወላድ መካን ሆኖ ሲሳደድ እና ሲገደል፣ በግፍ ከነነብሱ ጉድጓድ ሲጣል ሲቀበር፣ ማረፊያ አጥቶ ሲቅበዘበዝና የሰው ልጅ ይሸከመዋል ተብሎ የማይታሰብ ግፍ እና መከራ ሲደርስበት እርመኞች ከዘመናት በፊት የገደሏትን ኢትዮጵያ የሙት መንፈሷን ጣዖት በማምለክ፥ እንዲሁም የአመንዝራይቱ ኤልዛቤል ምሳሌ የሆነችውን እርም መሸለም ፤የሰመርናሃ ሰፋሪ አባ መላኩ (ፋኑኤል)አሳፋሪ ተግባርና ከትብብሩ ውስጥ መውጣት ባለመቻላቸው ህዝባችን ለባህርይው የማይስማማውን ጥቃት እና በደልን እንዲሸከም ትልቅ አስተዋፆ አበርክተዋል።

*በዚህ እርቅ በመጀመሪያ ከምንምና ከማንም በላይ እግዚአብሔር ይመሰገንበታል ፥በምስጋና መስዋዕት ይሸለምበታል !።*

*የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እርቅ ለእኔ አምላካዊ ምርቃት፤ ታአምር፤ገድል ነው። ለዶ/ር አብይ በጎነት ፣ለመልካምነት መሰናዳት ብሩክነትና ግልጽነትን ለተዋበ መንገዱ ብሩህ ነት እግዚአብሐር ለኢትዮጵያዊያን የሰጠን የመንፈስ ማረፊያ ብሄራዊ እርቅ ቀን ነው። ለዶ/ር አብይ በጎነት ፣ ለመልካምነት መሰናዳት፤ በመደመር ለተዋበ መንገዱ ብሩህነት እግዚአብሐር ለኢትዮጵያዊያን የሰጠን የመንፈስ ማረፊያ ብሄራዊ እርቅ ቀን ነው።" ለዚህም የዶ/ር አብይ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አዉደ ምህረት ላይ መመስገንና መሸለም ምንም ጥያቄ የለም ። የኢየሩሳለም ጋዳማትና በሌሎችም የሚገኙ መነኮሳት ለረጂም አመታት ለዘለቀው ጸሎታቸዉ ይመሰገኑበታል ምስጋናም ይገባቸዋል። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እርቅ ለእኔ አምላካዊ ምርቃት፤ ታአምር፤ ገድል ነው። ይህች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሁላችንም ነበረች ይህንን አጥተነው ነበር እናም፤ ከዘመናት በሁዋላ በአባቶች የሰላምና እርቅ አገኘነው ።እናመሰግናለን ዶ/ር አብይ ፤የእውነት አርበኝነት ። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን ታሪክ የቀደምቱን የሰማዕታት ተጋድሎ የፈጸመ የታላቅ መሪ ገድል ነው ታሪክ የሚዘከረው።*

*ከአስራሶስት አመታት እልህ አስጨራሽ የቤተክርስትያን አባቶች ለማስታረቅ በራሳችን ተነሳሺነትና በእግዚአብሐር በጎ ፈቃድ የተሰበሰብን ኮሚቴ አቋዋቁመን ጥረታች ን ቀጥለን ። ከአቶ መለስ ፤ከአቡነ ጳውሎስ ፤መቶ አለቃ ግርማ ፤አቶ ሀይለማሪያም ፤አቦይ ጽሃየ ወዘተ የሁሉንም በር አንኩዋኩአን ፥ወ/ሮ አዜብም አልቀሩን ሁሉንም ተማፅኖ አሰማን ደብዳቤ ጻፍን ፥ ለቤተክርስትያን እርቅ ሁሉን ም ምንጭ ተጠቀምን -እግዚአብሐር ይርዳችሁ ከሚለዉ የወ/ሮ አዜብ መፅናኛ ቃል በስተቀር ፤ለእርቅ ሁሉም ምንጮች ደረቆች ነበሩ። የሚረዳን አጥተን ኤሎሄ አልን ፤የሞተ የተረሳ ነበር ።እርቅ ማለታችን እንደ ተስቦ በሽታ ተቆጥሮብን ። እንዳዉም እርቅ የሚሉ ጣቶች ይቆረጣሉ ብለውን ነበር። ነበርም ቀላል ከሆነ። ያንን ዘመን ሳስብ ፤ስንቶች ይህችን በመደመር የተገኘ ች የቤተክርስትያን እርቅ ቀንን ሳያዩ ግን ተመኝተዋት አፈር እንደተጨአናቸው ሳስብ ሰዉ መሆን ያስጠላል ሁሌም አለቅሳለሁ ።በተለይም አቡነ ዜናማርቆስ ከአሜሪካ፤ አቡነ አብሳዲ ከኢየሩሳለም፤ አቡነ መርሃ ክርስቶስ ከትግራይ፤ አቡነ ሕርያቆስ ከኢየሩሳለም ሀገረስብከቶችና ሌሎችንም ኢትዮጵያዊያንን ወገኖቻችን ምዕመናን ሳስብ።*

*እርቅ ብለን ረቂቅ የውስጥ ጉዳቶች ተጎዳን ። ውስጣችን በእጅጉ ተጎሳቁሏል። ውስጣችን ዕንባ የከተመበት፤ ውስጣችን በሃዘን ብዛት የከሰለ፣ የጠወለገም ነበር ። ተስፋችን ጥግ አጥቶ በተሰደድንበት እየ መከርንበት የኖርን ፤ ለአንድ አመት ቆይታ ከአደረጉት አዲስ የኮሚቴ አባላት ጋር እነሆ ያን ራሃብ ቁጭ ብለን በጉባዔው ተሰይመን ትንሳዔውን አዬን፤ አዬሁት። ተላቀስን ... አነባን ። ቅጽበቱ እጅግ ይደንቅ ነበር። ትዕይንት ነበር የሚመስለው። እጅግ ይመስጣል። እጅግም ያጽናናል። እጅግም ይፈውሳል ተደራዳሪ አባቶች የሰሩት አኩሪ ሥራ የዘመናት ሃዘኔን በፍቅር እንባ አጥቦታል። በተለይ አቡነ አብርሃምን (የጎጃም ባህርዳሩን )አቡነ ጎርጎሪዎስን (የሸዋ )መችም ቢሆን አልረሳቸዉም ።እኔ በቤተክርስትያኔ እርቅ ትፍስህት*

ተሰምቶኛል። እኔ ሰናይ ተሰምቶኛል ። እኔ ፍሰሀ ተሰምቶኛል። እኔ ህይወት ተሰምቶኛል። እኔ መኖር ተሰምቶኛል።"ሰው ያሰባል እግዚአብሔር ደግሞ ይፈጽማል" ተፈጸመ። እግዚአብሔር ፈጸመው ይመስገን።

አባታችን ሙሴ ሞቶ ኢያሱ የአመራሩን ቦታ ወረሰና ሕዝቡ በእርሱ መሪነት እየተመሩ ኢያሪኮ ደረሱ፡ ከተማዋን ሲወሩ ከከተማዋ ያገኙትን ኢቃም ሆነ ምንም ነገር ንእዲያነሱ እግዚአብሔር "ከእርም ራሳችሁን ጠብቁ፤ እርም ነውና አንዲች ነገር ኢታንሱ" (ኢያሱ 6፡18) ብሏቸው ነበር፡፡ የእኔ ቢጤ ደካማ አካን የሚባለው የከርሚና ⍰ ንባሪ ላጅ በስስት የተበከለ ሕሊናው አሸንፈውና እርም ከሆነው ነገር ወሰደ፡፡ በእርም ጉድጓድ ውስጥ ወደቀ፡፡ በእርሱ እርም ንክኪ የእግዚአብሔር ቁጣ በኅብረተ ሰቡ ሊይ ነደደ፡፡ ኅብረተሰቡንም ይዞት አዘቅት ውስጥ ገባ፡፡ (ኢያሱ 7፡1 ) ይህ አካን የተባለዉ ግለሰብ በፈጸመው የእርም ንክኪ ሁሉም ተዋረዱ፡፡ በሚቃወሟቸው ሰወች ተመቱ፡፡ ከአካን ጋር የተሰለፉት ሁሉም የድሉን አቀበት ሊወጡት ቀርቶ እንደ አፋፍ ሊይ ደንጋይ የእተናዱ ቁልቁለት ወረዱ፡፡ ከፈጣሪና ከአካባቢው እርዳታ ሊያገኙ ቀርቶ የገዛ ልባቸው ጥሎአቸው ቀለጠ፡፡ (7፡5) ኢያሱም እርም በኅብረተሰቡ መካከል እንደገባና በርእሙ ምክንያት እርሱም ኅብረተሰቡም እንደተመቱ ተነገረው፡፡ እርሙ ቁልቁል እንደለቀቃቸውና እንዳዋረዳቸው ተረዳ፡፡ በግንባሩ ወድቆ ማልቀስ ጀመረ፡፡ እግዚአብሔርም የኢያሱን እንባ ተቀበለና "አብሮህ የተሰለፈው ሰራዊት በእርም የተበከለ ነው፡፡ እርምህን ካላወጣህ በመካከላችሁ አልሆንም፡፡እናንተም መቋቋም አትችሉም" (7፡12-13) ሲል ከገቡበት እርም መውጫ መንገድን ነገረው፡፡ ኢያሱ ይህን ሲረዳ እርም ተሸክሞ ከሰልፉ ገብቶ ውድቀት ያመጣውን ሰው ከመካከሉ አንቆ አወጣው፡፡ ሕዝቡ ሁሉ በደንጋይ ወግረው፤ በሳት አቃጠለው፡(7፡25) ከዚያ በኋላ ነበር እግዚአብሔር ኢያሱን "አይዞህ አትፍራ አትደንግጥ ሰሌፈኞችህን ሁሉ ከአንተ ጋር ውሰድ፡፡ ተነስተህም ወደ ጋራ ውጣ፡፡ አሁን ድሉን ሁሉ ሰጥቻህለሁ" አለው፡፡ ስለዚህ አገሬ ኢትዮጵያም እርም የከበዳት አገር ነችና ፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያንም የእርም ንክኪ ሰቃይ ላይ ነችና ቅዱስ ሲኖዶስ ፤ ሁሉንም ኢትዮጵያዊ በሚያዋህድ መደመር የበኩሉን እርምን እንደወረርሸኝ በሽታ የሚያሰራጨትን ለማስቆም ይችልና ኢትዮጵያም ከእርም ንክኪ ቁጣ ትወጣ ዘንድ መንፍሳዊ ሀሊፊነት ከፊት ለፊትታ ተደቅንዋልና መፍትሄ ይሻል ።

ይህ ድራማ ከእርመኞች ቲያያትር ቤት ወጥቶ በኢትዮጵያ ዉስጥ እየተሺከረከረ እንደ ብሄራዊ ባህል የሆነዉ የገደለንን አገር ላይ ፤ኢትዮጵያ ላይ ፤ያመጸን ፤የከዳን ፤ባንዳ ማክበርና ማባባል የሆነ ትያትር ወይንም ድራማ ነዉ ። በዚህ ቡትቶ ትያትር ህዝቡ ተሰፋ የጣለበት ራኢይ እንዲጨልም እየሆነ፤ የወደፊቱ ጉዟችን ተሰፋ በሰመርናሃ ሰፋሪ አባ መላኩ(ፍኑኤል) ለእርመኝነት ሲያላዊ መቅሰፍት ህጋዊ ፈቃድ ሽልማት መጨለሙ በገሀድ ኢታየ ነዉ። ዛሬ በቤተክርስትያን ምን እየተሆነ እንደሆን መረዳት ይከብዳል።በህዝብ ላይ ከፍተኛ በደልና ዘረፋ የፈጸመ፤ የማንነት ምድሩን አሳልፎ ለባእድ በመስጠት የዜጋን ህይወት በማስቀጠፍ ከጠላት ጋር በማበር ቀጥተኛ አመራር በመስጠት የተሳተፈ መሆኑ እየታወቀ ፤ በዶ/ር አብይ የአመሪካ ጉብኝት ዋሽንግተን ዲሲ ፤ካሳ ተ/ብርሀንን በዶ/ር አብይ ፊት የቀረበበት ከአንባሳደርነቱ ይነሳ አሰደንጋጭ የህዝብ ተቃቅዉሞና ቁጣ እየታወቀ፤ የሰመርናሃ ሰፋሪዉ አባ መላኩ(ፋኑኤል) ቁጭ ብለዉ ኢያዩ ፤በተደጋጋሚ በዲሲ የኢትዮጵያ ኢምባሲ የሰልፍ ተቃዉሞ ሳይዘነጋ፤ ሰዉ እንደጠፋ ሁሉ እርመኞች በካባ ሸፋን እስከ መርዛቸዉ ገብተዉ እንዲያቦኩ ከተፈቀደ እንደ ተበዳይ ኢትዮጵያዊ ሚዛን ሰናየዉ ልባችን አዝኗል። አማራ ኢትዮጵያዉያን በአባይ ሰኳሬና በካሳ ተ/ብርሃን ነፃነታቸው ሲገፈፍ፤ማንነታቸው ሲፋቅና የመኖራቸው ህልውና በሞት ጥላ ስር ሲወድቅ ለአማራ

*ኢትዮጵያዉያን ሞት ተጠያቂ ጉዳዮችን መሸለም ዕዳውን ያከብድባችኋል ። ሌሎች እርመኞች እየታደኑ ባለበት ካሳ ተ/ብርሀንን መሸለም ከተጠያቂነት አያድንም። ካሳ ተ/ብርሃን ከለሎች በምን ይለያል? ወንጀለኞች ወንጀላቸዉ ያለ ህግ ተፍቆ ፤ቀደም ሲል የያዙትን እንዲያዙ ሳይሳቀቁ ተንደላቀዉ መሸለም ሕይወት ባጣዉ፤ በሞተዉ፤ በቆሰለዉ፤ አካሉ በጎደለዉ፤ ቤተሰብ አገርና መሬት አልባ ባደረጉት፤ ከነ ስቃዩ ባለዉ እንዲሰደድ ባደረጉት የአማራ ኢትዮጵያዊ ህዘብ ላይ መቀለድ ይሆናል ፥ ለእርመኞች አጥንት ለበሳዉ ግፋቸዉ የበተክርስትያን የቀኖና ኢቃ በአዉደ ምህረት ለእርመኝነት ሲያላዊ መቅሰፍት ህጋዊ ፈቃድ መስጠት ።ወይ ዘንድሮ ! ምን አይነት ትያትር ነዉ!፤*

*ለመሆኑ የሰመርናሃ ሰፋሪዉ አባ መላኩ(ፋኑኤል) ይህንን ለማድረግ ምንስ ፥ሞራል ይኖርዎታልን? በአገሬሳለሁ እምነቴን በነገሩኝ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን አባቶች አገላለጽ ፤ "ሲሞንያ "አያደርግዎትም ወይ? የሲሞናዊ ባህርይስ አይሆንብዎትም እንዴ..? ማለትም ፓትሪያርክ ብፁዕ አቡነ ማትያስ ፤ ሲሞናዊ ብለዎታልና መጀመሪያ ከዚህ የከበደ ጉዳይ ራስዎትን ነጻ ማዉጣት ይጠይቃል፤ "ክህነት መግዛት እርም ነዉና "። በሌላ አገላለጽ ፥ በሃዋርያት ሥራ 8፣18 ሲሞኦን በሀዋርያት እጅ መጫን መንፈስ ቅዱስ እንዲሰጥ ባየ ጊዜ ገንዘብ አመጣላቸዉና እጀን የምጭንበት ሁሉ መንፈስ ቅዱስን ይቀበል ዘንድ ለእኔ ደግሞ ይህንን ስልጣን ስጡኝ አለ። ሃዋርያዉ ቅዱስ ጴጥሮስ ግን እንዲህ አለዉ፥ የእግዚአብሔርን ሥጦታ በገንዘብ እንድታገኝ አሰበህልና ብርህ ካንተጋር ይጥፋ፤ ልብህ በእግዚአብ ሔር ፊት የቀና አይደለምና ከዚህ ነገር ዕድል ወይንም ፋንታ የለህም አለዉ። ይላልና የእግዚአብ ሔር ቃል ፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ በዚህ ጉዳይ ላይ የቅዱስ ጴጥሮስን ሃዋርያዊ እርማ ያነሳል ዉይንስ እርምም ላይ ነዉ? ወይንስ ባልጸፍ በወደድኩ ። ግን ያበጠው ይፈንዳ እንጅ እጽፋታለሁ። በስንቱ ታፍኘ እዘልቀዋለሁ በማለት ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ እንዳሉት አባ መላኩ (ፋኑኤል)" አዲስ ተክል "ገና ያልበሰሉ አማኝ ብሎ እስኪበስሉ እየጠበቀ ?*

*እርመኛን እርመኛ ሊሸልም በግሉ መብቱ ነዉ ። ዳሩ ግን በቤተክርስቲያኔ በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አዉደ ምህረት ላይ የእርመኞች በካባ ሸፋን እርኩሰት ግን የእምነቴ ጉዳይ ነዉና አልደራደርበትም ስለእግዚአብ ሔር ፤ ስለ ወላዲተ አምላክ ብላችሁ አቁሙ እያልኩ አብዝቸ እጮሀለሁ። የ27 አመት የእርመኞች የግፍና የአፓርታይድ አገዛዝ በሰመርናሃ ሰፋሪዉ አባ መላኩ(ፍኑኤል) የእርመኝነት ሸልማት አሣዛኝና አስገራሚ ክስተት ሆንዋል ለነጻነት ፈላጊ ኢትዮጵያዉያን ሕይወት ። የአብነት ት/በቶች እየተዘጉ ፤በገጠር አቢያተ ክርስቲያናት ካባ ጠፍቶ በሴት ቀሚስ ይቀደሳል፤ በሴት ሣንጥላ ታቦት ይወጣል፤ መገበሪያ ጠፍቶ ስብሃተ እግዚአብሄር እየተስተጉዋጎለ ቤተክርስቲያናት እየተዘጉ ፤ ያሉትን ማስተዋል በተገባ ነበር። ነገ ደግሞ እድሜ ከሰጠን ውሉ እንደ ጠፋበት ልቃቂት ለተወሳሰበው ችግር ፈጠሪነታቸው ገና ፅላት እንዳይቀረጽላቸው፣ መልከአ ገድል እንዳይጻፍላቸው ያስፈራል። ከንቱ ውዳሴ መንበረ ሰላሴን ፐትርከናን እንደሚያስመኝ ከከፋት ልጆች ሁሉ አባት ከዲያቢሎስ የታየ ሃቅ ነው። ከንቱ ውዳሴና እብሪት ከፉ ነው።የነገውን ለማወቅ ደግሞ ነብይ መሆንን አይጠይቅም።*

*እጅግ የሚያሳዝነኝ እዚህ የእርመኞች ሸልማት የተገ ኙ"የምናከብራችዉ አገር ወዳድ " እነሱን ተከትለዉ በሀሳባቸዉ ወሰንና ግዛት ያሰመሩ ተከታዮቻቸዉም አዝነዋል ። በየደረጃዉ በነቀዘ ህሊናቸዉ ራሳቸዉን ለአገር መሬት ስርቆት ላመቻቹ የተከተሉት መንገድ በማንኛዉም ወገን ለሸዎች ሞትና ስደት ለዳርጉት ግፈኛ እርመኞ ች ሸልማት ተገኝተዉ ማጨብጨባቸዉ አሳፋሪና ከምናከብራችዉ የማይጠበቅ ነዉ ፤ታሪክ ይቅር የማይለዉ ።ኢትዮጵያውያን ተደምረን የአንድ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ህዝብ መሆናችንን የምናሳይበት*

*ዉህድ ምልክት ከእርመኞች ጋር ህብረት በመፍጠር ከቶ ሊሆን አይችልም ።በሕዝባቸው መከራና ሰቆቃ ለመክበር ሰልፋቸውን ያሳመሩ ከሰዋዊ ባሕርይ አፈንግጠው አውሬነትን እየተለማመዱ ያሉ ከሰው መሰል ጨካኞች መዋረድን በማስቆም እንጅ ። የሰመርናሃ ሰፋሪዉ አባ መላኩ(ፋኑኤል) በህግ አምላክ በሰንደቅ አላማዉ!።*

*ማሳሰቢያ፥ ይህ በቤተክርስትያን ጨዋ ምግባሩ የምናዉቀዉን አቶ ረታን አይመለከትም*

*"እግዚአብርሒ በአንድ መንገድ በሌላም ይናገራል። ሰው ግን አያስተውለውም።"* (መጻሐፈ እዮብ ምዕራፍ ፴፫ ቁጥር ፲፬)

*ኢትዮጵያ ለዘለአለም ትኑር !!!*

*ገብርኤል ብዙነህ*

*ማሳሰቢያ፥ ይህ በቤተክርስትያን ጨዋ ምግባሩ የምናዉቀዉን አቶ ረታን አይመለከትም እንዳዉም ይደልዎ ይገባል ብለናል። Dec 2018 ( ይቀጥላል....)*

